**ኢትዮጵያን ያለብሔሮች የሚፈልጓት ያፈርሷታል!**

**Nation**: large aggregate of people united by common descent, culture, or language, inhabiting a particular territory.

**Tribe**: A social division in a traditional society consisting of linked families or communities with a common dialect.

**Clan**: a group of close knit and interrelated families/offspring.

በኢትዮጵያ እስከ አሁን ከገዙዋት ገዥዎቹዋ አንድም ገዢ ወይንም የፖለቲካ ስርዓት ለኢትዮጵያ ብሔሮች ኖረው እንደማያውቅ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ግልጽ አድርገው ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ኖረው ያለፉት አንድም ለመንግስታቸው ያለገደብ ገዢ ሆኖ መኖር ስሰሩ በሌላ በኩል በዙሪያቸው ለኮለኮሏቸው መሳፍንቶችና ለ”ንጉሳውያን ቤተሰብ ” ምቾት ብቻ ነበር ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር የሚያስችል ታሪክ ድሪቶ የተከናነበች ሀገር ናት ኢትዮጵያ፡፡ ይህም ማለት በተለያዩ ጊዜያት እራሳቸውን የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት/አስተዳዳሪ ብሎ የሰየሙ አምባገነን ገዢዎች የነገሱትና የኖሩት በኢትዮጳያ ስለምኖሩት ብሔሮች እና ብሔረሰቦች እኩልነት ፣ ስልጣኔ እና ብልጽግና ሳይሆን ስለራሳቸውና ብሔሮችን ገፍተው ለራሳቸው ኑሮ፣ ለእርሻ እና እርባታ ምቹ የሆኑ የመሬት ክፍል ተስፋፍተው እንደኖሩ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

የዘመናዊቷን ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ንጉስ አፄ ምኒልክን አይተን እንደሆነ በየአከካባቢው የሰፈሩትን ብሔሮችን እኩልነትና ስልጣኔ ለማምጣት አቅደው ሳይሆን ሰፊ ሀገርን የማስተዳደር ፍላጎት ብቻ መሰረት በማድረግ አያሌ የአካባቢውን ብሔሮች አስጨነቀው ከመግዛታቸውም በላይ የብዙ ንፁኸንን ደም በግፍ እንዲፈስ ምክንያት ሆኖ አልፈዋል፡፡ ከዛም አልፎ የመኳንንቱንና የመሳፍንቶችን ከህዝብ በላይ ከፍ አድርገው በመጠበቃቸው ምክንያት የህዝብ ስቃይ እየባሰ እንደሄደ የተለያዩ የንጉሳውያን ጊዜ ታሪክ ድርሳናት የሚያሳዩት እውነት ነው፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጊዜ ክልል ውስጥ በየአካባቢው የነበሩትን ነባር ብሐሮችን ከየሰፈሩበት አካባቢ(መሬት) በማባረር ሰፊው ህዝብ የስቃይ ኑሮውን ስገፋ ጥቂቶች የተቀማጠለ ህይወት ሲኖሩና የብዙችን ስቃይ የሚያበዙ የንጉሱ ወታደሮች ነባሩን የአካባቡን ህዝብ ለማጥፋትና በምትኩም (አሁንም አንዳንዶችን እንደያዙት አቋም) የአንድ ቋንቋ፣ የአንድ ሀይማኖት ሀገር አድርገው ኢትዮጵያን ጠፍጥፎ ለማበጀት ሞክሮ እንደነበረም ጭምር ይታወሳል፡፡ ከአፄ ምንሊክ ህልፈት በኋላ ወደ መንበረ ንግስና የመጡት ተፈሪ መኮንንም (በኋላ አፄ ኃይለስላሴ) የቀድሞውን የአባቶቹን ፈር በመከተል የየአካባቡን ነባር ህዝብ ስቃይ ተባብሰው እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡ ብሔሮች ለሰፈሩበት መሬት እንኳ ለኢትዮጵያ ብሔሮች ነፃነትና እኩልነት ዴንታ የለሌው የአፄ ኃይለስላሴ ስርዓትም የኤርትራ ህዝብን ንቆ መሬታቸውን ግን በፍቅር ስለወደዱ ተጨፍልቀው በዘውዳዊው ስርዓት እንደ ሁሉም ኢትዮጵያ ብሔሮች እንዲተዳደሩ ሲያደርጉ ከጥቂት አስመሳይ “ኢትየጵያ ወይ ሞት” አጀንዳ አራማጆች ጋር ተመሳጥረው ሲጨፈለቁ ስለዚህ ጉዳይ የኤርትራ ህዝብ አቋም ምን እንደሆነ ለማወቅ አልፈለጉም፡፡ ፍላጎታቸው የነበረው ግዛታቸዉን ማስፋፋት ነበርና ህዝቡንና ፍላጎታቸውን ማዳመጥን እንደ ጊዜ ማጥፋት ቆጥረዋል ፡፡ በውጤቱም ተጎዳው ብሎ የተነሳው የኤርትራ ህዝብ ዛሬ በምን አይነት ሁኔታ ውስጥም ይኑር ለፍላጎቱ ብዙ ወጋ ከፈለና ለመገንጠል በቃ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ንጉሱ አጤ ኃይለስላሴ በኦሮሚያና ደቡባዊ ኢትዮድያ አካባቢ የሚኖሩትን የመሬት ባለቤቶችን በመግፋትና በማፈናቀል መሬታቸውን የንጉሱና የንጉሳውያን ቤተሰቦች መፈንጫ በማድረጋቸው ነባሩ የመሬት ባለቤቶች ግን ባሪያና ፍፁም የሰው እጅ ተመልካች አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሲዳማና በሌሎችም አካባቢዎች በመንቀሳቀስ የአካባቢውን ነባር የመሬት ባለቤቶችን አፈናቅለው ንጉሱና የንጉሳውያን ቤተሰቦች የመኖሪያ፣ የመዝናኛ እና የእርሻ ቦታ አድርገው በመከፋፈል የአካባቢውን ነባር የመሬት ጌቶችን የበይ ተመልካች አድርገውት ለረጅም ዘመናት ዘልቀዋል፡፡ በዚህም ለራሳቸውና ለቤት እንስሳቶቻቸው ሁሉ ሳይቀር የመሬት ነባር ጌቶች የማይኖሩትን ሰማይ የነካ የተቀማጠለ ኑሮ ኖረዋል፡፡ ከዚህያም አልፎ

በጭቁኖች መሬት ላይ በእርሻና በኩባንያዎች በሽርክና የሚያገኙትን ረብጣ ትርፍ መሰብሰብ መደበኛ ስራቸው ከመሆኑም በላይ በአለም አቀፍ ታዋቂ ባንኮች ውስጥ በብርና በወርቅ ሰውረው አስቀምጠዋል፡፡ ዛሬ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸውም አባቶቻቸው ከጭቁን ህዝብ ዘርፎ ባስቀመጡላቸው ሀብት ላይ እመነዘሩ አለማቸውን ሲቀጩ ሲኖሩ በአንፃሩ ደግሞ ብዙሐኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች እስካሁን ድረስ ገና ነፃነቱን እንኳን መጎናፃፍ አልቻለም፤ ከእኮኖሚ መላሸቅና ከድህነት ማነቆ መላቀቅ አልቻለም፡፡ ከዚህ በላይ መሬትን(መስፋፋትን) ከሰው ልጅ የማስበለጥ አባዜ ከወዴት ይገኛል?

መጀመሪያም የነዚህ ገዥዎች ዓላማ የኢትዮጵያን ብሔሮች ከድህነት አረንቋ አውጥተው ወደ ብልጽግናና ስልጣኔ ማማ ማውጣት ሳይሆን የኢትዮጵያን ነባር ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በራብ ጠኔ እያለቁ ገዥዎች ለራሳቸው በተስፋፉ መሬት ላይ እንሸስት በማድረግ ከሚያገኙት ትርፍ ሁሉም እንደነሱ የጠገበ እስክመስላቸው ላይራቡ ጠግበው ኖረዋል፤ ዛሬም መልካቸውን ቀይረው እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ የሚያገኙት ትርፍና ምቾት የተሞላበት ኑሮ ያሳወራቸውና አንዳንድ ከሀብታቸው ላይ መነሳትን ያልፈለጉ መኳንንቶችና መሳፍንቶች የያዙትን አካባቢ ላለመልቀቅ በተለይም የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮችን መሬት በመቀራመት ያፈሩትን ለማዝለቅ ያ "ከፉ" ደርግ መተው "መሬት ላራሹ" አዋጅ ሲያውጅባቸው "ንጉሳውያን" እስከዚያ ድረስ የሚፈልጉት የብሔሮችን ነፃነት ሳይሆን ብሔሮች ቀደም ብሎ ያረፉበትን መሬት ነበረና የንጉሱ ስርዓት በደርግ መገርሰሱን ተቃውመው "የይሁዳ አንበሳ…" በሚል ተደራጅተው ከመታገላቸውም በላይ የሲዳማና የኦሮሞን መሬት መቀራመታቸውን ለማስቀጠል ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ ከንጉስ ስርዓት በኋላ እስከ አሁን ድረስ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግስታትም የራሳቸውን የስልጣን በላይነት ለማረጋገጥና የህዝብን ሀብት በተራቸው ለመዝረፍ ተዘጋጁ እንጂ ለተበደለና በግፍ ለተጨፈጨፈ ህዝብ ምንም አልፈየዱም፤ ይልቁንም ይበልጥ ችግራቸው ላይ ችግር እየጨመሩ መከራቸውን አባባሱ እነጅ፡፡ በኢህአዴግ ስልጣን ዘመንም የምናየው በአንድ በኩል ስልጣኑን እስከወዲያኛው ለማስጠበቅ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የአፈና ቀንበር ስጭን በሌላ በኩል ደግሞ በሀገርቷ አራቱም ማዕዘናትና መሃል ሀገር የራሱን ቅርቦች አንቀሳቅሰው እንዲነግዱና እንዲዘርፉ ፈቅደው የየአካባቢውን ህዝብ በራሳቸው ቀዬ ለማኝ ሆኖ እንዲቀሩና በራብ የሚገረፉና የሚረግፉ አድርገዋቸዋል፡፡ እያደረገም ይገኛል፡፡

በየጊዜው እየተፈራረቀ ብሔሮችን በአጥንት የሚያስቀረውን ስርዓት ለመታገል የተለያዩ ክልላዊና ሀገር አቀፍ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ህዝብ አዋጭ ነው ብሎ ባመኑበት በሰላማዊ መንገድ እየታገሉና እያታገሉ የሚገኙ (ድከመታቸውና ክፍተታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ ነፍጥ አንስተው ዱር ቤቴ ብሎ ይገኛሉ፡፡ በረሃ የመሄድ ፋይዳ ከሀገር ጥቅም አንፃር ያለው ፋይዳ እይታ እንደተጠበቀ ሆኖ በረሃ የገቡትም ሆነ በሰላማዊ መንገድ ሀገር ውስጥ የሚታገሉት ታጋዮች እንቅስቃሴ የሚያሳየው በኢትዮጵያ የአፈናና የዘረፋ ተግባር እየተወራረሰ በህዝቡ ላይ የሚፈፀመው ግፍ ለከት ከማጣቱም በላይ እስከ አሁን ያሉት ገዥዎች ፍላጎታቸው የኢትዮጵያን መሬት ከመቀራመት ያልዘለለ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ እጅግ የሚያሳዝነውና በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ተማርን ከሚሉ ሰዎች በማይጠበቅ መልኩ በቀጣይነትም የብሔሮችን መብትና ነጻነት መሰረት ያደረገና ብሔሮች ተባብረው የገነበዋት ኢትዮጵያ እንዲትፈጠር የማይፈልጉ ግትር ሰዎች መኖራቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም ነገር በየጊዜው በዜሮ የማብዛት ነገር አድርጎታል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ማዓቶች ብሔሮች ላይ መፈፀሙንና እየተፈፀመ እንዳለ የተነገራቸው፣ ያነበቡና ኖረው ያዩ ሰዎች በኢትዮጵያ በብሔር መደራጀትና የየብሔሮቹ አባላት ለፍትህና ሰላም መስፈን ህዝባቸውን በቅርበት በመገኘት ማንቃትና ለትግል ማንቃሳቀስ ራስ ምታት ሲሆናቸው እነዚህ አባቶቻቸው የነገሩዋቸውን ጥብቅ ምስጥር በልባቸው ይዘው እስከ አሁን ድረስ ከሚበደለው ብሔርና ብሔረሰብ ይልቅ ይጠፋል ብሎ ስለምሰጉት(በመገንጠል) መሬት በብሔር የተደራጁትን ከመውቀስም አልፎ አፍ አውጥተው መሳደብ ጀምረዋል፡፡ ከዛም አልፎ ብሔሮችንና ብሔረሰቦችን ለማንኳሰስ ስለፈለጉ ብቻ "ጎሳ" እያሉ ይጠራሉ፡፡ ከነዚህ የብሔሮችን እኩልነትና ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፈነባትን ኢትዮጵያን እንደገና ተባብረው መገንባት ሳይሆን ብሄሮች የሰፈሩባቸውን መሬት (ብሔሮች ባይኖሩም ሰፊ የኢትዮጵያ ቆዳ ስፋት) ከምፈልጉት መካከል ፕ/ር መሳይ ከበደ ግንባር ቀደም ከመሆናቸውም በላይ የብሔርንና የ"ጎሳ" ልዩነቶችን ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብሎ የሚጠበቁ ሰው ብሔሮችንና ትግላቸውን

ለማንኳሰስ ስለፈለጉ ብቻ “ጎሳ”፣ የ“ጎሳ” ፓርቲዎች በማለት የሚጠሩና ያወቁትን ለመናገርና ለመጻፍ እንኳን ያልፈቀዱ ሰው መሆናቸው ነው፡፡ እኚ ምሁር “መድረክ የፖለቲካ አስመሳይነት መጨረሻ?” ብሎ በሎም መጽሔት ላይ በሚያዝያ 24/2006 ዓ.ም በወጣው ጽሁፍ ብሔሮችን ሳይሆን ብሔሮች የሰፈሩበትን አካባቢ እንዳያጡ ስጋት እንዳደረባቸው የሚያሳብቅባቸው ጽሁፍ በመድረክ አላከው አስነብቦናል፡፡ በጽሁፋቸውም ፍጹም ምዛናዊነት በጎደለው መልኩ መድረክ አንድነትን ስላገደ ብቻ አስገንጣይና “አስመሳይ” ብሎ ፈርጀው በአንጻሩ ደግሞ አንድነትን ወደር የማይገኝለት “ጠንካራ” ድርጅት እንደሆነ የተንሻፈፈ ብይን ሰተዋል፡፡ ውሳኔው የራሱ የግሉ ቢሆንም የምሁሩን ምዛናዊነት ግን ጥያቄ ውስጥ ይከታል፡፡ ፍጹም ግልብና ምክንያት አልባ ስሜታዊም ያደርገዋል፡፡ ፕሮፌሰሩ ዘገዩ እንጅ መጀመሪያም ኢትዮጵያን (አንድነትን) ሽፋን አድርገው የሚሯሯጡ ጥቂቶች ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም ፕ/ሩ ግን ለየት የሚያደርጋቸው በድፍረትና በግልጽ ጭቁኖቹን ብሔሮች ለምን እንደ ድሮ ዝም ብላችሁ አትገዙም/አትሸጡም ማለታቸው ሲሆን ይህም ከአንድ ከተማረ ሰው የማይጠበቅ ዉሳኔና ብሔሮች ስለመብታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ በልጆቻቸው አማካይነት እያወቁ መሄድ በሂደት (ምናልባት እነ ፕ/ር ስልጣን ላይ ስመጡ) የመዝረፍ እድል ይጠባል ብሎ የተናደዱ ያስመስልባቸዋል፡፡ የኢህአዴግን ህገ-መንግስት አንቀጽ 39ን በተመለከተም ለመድረክና አንድነት ሰጣገባ ምክንያት ባይሆኑም ፕ/ሩ ግን መድረክ መገንጠልን ይሰብካል ብሎ ከመናገርም በላይ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በአስተዋይነት የተናገሩትን አባባል በቁጣ ስለተሞሉ ብቻ ትክክል እንዳይደለ አድርገው ለመኮነን ብዕራቸውን አንስተዋል፡፡ ዶ/ር ነጋሶ “መገንጠልን እቃወማለው ነገር ግን የመገንጠል መብትን እደግፋለው” ማለታቸው ምኑ ላይ ነው ስህተቱ? ፕ/ር መሳይስ ቢሆኑ አንድ ቀን ሀገርቷን የግዛት እድል ቢያገኙ የብሔሮችን መረገጥና መገፋቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰፊ የኢትየጵያን ግዛት ለማቆየት ብቻ ይሰራሉ ማለት ነው?

መቼም የተረገጠና የተገፋ ብሎም በሀገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ የተቆጠረ ህዝብ በህገ-መንግስት ውስጥ የመገንጠል መብት ኖረም አልኖረም ከተበደለ ነጻነቱን መናፈቁ ስለማይቀርና እያየ ካለውም ጭቆና ነፃ ወጥተው የሚያየው ጭቆና እምንት ነው ብሎ ማሰባቸው አይቀርም፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በሀገርቷ ዴሞክራሲና ፍትህ ቢሰፍን፣ የሀገር ሀብትና ስልጣን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ ቢሆን ብሔሮች ሁሉ በመስማማትና በመፈቃቀር አንድነታቸውን አጠናክረው ይኖራሉ እንጂ በህገ-መንግስት መገንጠል ተፈቅደዋል ስለተባለ ብቻ ብድግ ብሎ አይገነጠሉም፡፡ ምክንያቱም ዴሞክራሲና ፍትሕ በሰፈነበት አንድነት መዝለቅ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ የሚያውቁበት ከፍተኛ ንቃተ ህሊና ደረጃ ይደርሳሉና ነው፡፡ ስለዚህ የመገንጠል መብት ከህገ-መንግስት መሠረዝ ለኢትዮጵያ አንድነት ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ይሄ ነው እንግደህ የዶ/ር ነጋሶ ግዳዳ አመለካከትም የሚመስለው፡፡ መሆንም ያለበት እንደዛ ነው፡፡ እንደ ፕ/ር መሳይ ከበደ ከሆነ ደግሞ የኢትዮጵያ መሬት ከሚቆረስ የኢትዮጵያ ብሔሮች ለዘላለም በድንቁርናና በስቃይ ይኑሩ አይነት እንድምታ ያለውን ጽሁፍ በመድረክ አላከው አቀረቡልን፡፡ ለዚያም ይሆናል እስከነአካተው በኢትዮጵያ ጭቁን ብሔሮች ስለመኖሩም በልባቸው ከደው በብዕራቸው ያሳወቁልን፡፡ እዚህ ላይ አንባቢ እንዲረዳ የሚፈልገው በኢህአዴጉ ህገ-መንግስት አንጽ 39 ላይ የተደነገገውን የመገንጠልን ሀሳብ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም ብቸኛ መፍተሄ ነው ብሎ አያምንም፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ አፈናና ስቃይ ከ100 ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል፡፡ በዚህ ስቃይ የኖረና እየኖረ ያለው ህዝብ ደግሞ ከዚህ ስቃይ የሚበልጥ ስቃይ ይኖራል ብሎ ስለማያስብ ህጉ ተደነገገም አልተደነገገም አማራጭ ጎዳና መፈለጉ አይቀርም የሚል እምነት አለው፡፡ ስለዚህ ሕወሓት ለራሱ ብሎ ያስቀመጠውን ህገ-መንግስት አንቀጽ 39 ዙሪያ ክብ ሰርተን በማውገዝ እና በመቃወም ብሎም “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር” በሚል የምኞት ኑሮ በመኖር ሳይሆን ኢትዮጵያ የሚትኖረው ብሔሮች መገንጠልን /ነጻነት እንዲናፍቁ ያደረጋቸው ነገር ምንድር ነው ብሎ በሆደ ሰፍነት በማሰብና ለብሔሮች እኩልነት ተጨባጭ ዋስትና የሚሆን የመፍትሔ ሀሳብ ይዞ በመቅረብና ለውጤታማነቱም በመታገል ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በብሔር የተደራጁ ድርድቶችም ማድረግ ይችላሉ፡፡ ፕ/ር እንዳሉት የሀገር ህሊውና በሀገር አቀፍ ፓርቲነት ስም ፍቃድ አግኝተው በተግባር ግን በአንድ ብሔር የተደራጁ “ህብረ ብሔራዊ” ድርጅቶች ብቻ አይደለም የሀገር ህሊውና የሚረጋገጠው፡፡ተባብረው ቢሰሩ ደግሞ ይበልጡኑ ለሀገር እጅግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ፕ/ር ካሁን በኋላ ከ”ጎሳ” ድርጅቶች ጋር ተባብረው መስራት ”ከሳራ ነው፡”ብሎ” ህብረብሔራዎቹ” ግን የኢትዮጵያን ብሔሮችን የገፋ ፖለቲካ ስርዓት እንዲመሰርቱና ሀገርቷን እንደቀድሟቸው እንዲቆጣጠሩ ፍላጎቱ እንደሆነና በዚህም አቋም መጽናት እንዳለባቸው መክረዋል፡፡ ግን አፍራሽ ነው፡፡ ብሔሮችን የገፋ ኢትዮጵያ ፖለቲካ መፈለግ መጨረሻው መበታተን ይሆናል የሚል ስጋት ይፈጥራል፡፡ “የጎሳ ድርጅቶች ህዝብን ማንቃት አልቻሉም” ቢሉም ከፕ/ሩ ጽሑፍ መረዳት እንደሚቻለው

የብሔሮች መንቃት ክፉኛ እንዳስፈራቸው ነው፡፡ ፐ/ር መሳይን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንደዛ የደነገጡ በቤታቸውና በድርጅቶች ውስጥ የተሸጎጡ ብዙዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በግንቦት 8/2006 ዓ.ም በወጣች ሎሚ መጽሔት ላይ አንድ እራሱን የደበቀ አቶ/ወ/ሮ/ሪት ድብቁ ”የጎሳ ፖለቲካዊ አራማጆች የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ፎርሙላ” በሚል አርስት ስር በከተበው ጽሑፍ ብሔሮች ላይ ያለውን ጥልቅ ጥላቻ ለማንጸባረቅ ሞክረዋል፡፡ ከመነሻው ለመግለጽ እንደተሞከረው በብሄርና በጎሳ መካከል ሰፊ የትርጉም ልዩነት ያለው ብሆንም እነዚህ በብሔር ጥላቻ ተግፋፍተው የሚጽፉ ጻሐፊዎች (ተሳዳቢዎች) ከብሔር ፖለቲካ መሪዎች በላይ በብሔሮች ያላቸውን ስር የሰደደ ጥላቻቸውን ስለምያንጸባርቁ ኢትየጵያን ከመጥቀም እየጎዱ፣ ብሔሮችን ከማቀራረብ ይልቅ እያራራቁ  እያወቁ አያውቁም፡፡ የትኛው ድርጅት ነው በጎሳ ተደራጅተው እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ድርጅት? መዐህድ? አፍኮ? ...?

ለምሳሌ መዐህድ(የመላ አማራ ህዝብ ድርጅት) ከስሙ ለማወቅ እንደምቻለው የአማራን ህዝብ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በማጉላት ከሌሎች አቻ ድርጅቶች ጋር ለሀገር አንድነት የሚሰራ የብሔር ድርጅት እንደሆነ ነው የሚታወቀው እንጂ የጎሳ ድርጅት ሊባል አይችልም፡፡ ከዚህ ውጭ የወሎ ጎሳ ፖለቲካ ድርጅት፣ የጎጃም ጎሳ ፖለቲካ ድርጅት፣ የጎንደር አካባቢ ነጻ አውጪ ፖለቲካ ድርጅት ካለ ሊያስብል ይችል ይሆናል፡፡ ካልሆነ ግን መዐድን የጎሳ ድርጅት ማለት ከድርጅቱ መሪዎች ባሻገር ህዝብን እየነቀፉ መሆን አለበት፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት ተመኞች ኢትዮጵያን እንገነባለን እያሉ በተግባር ግን እያፈረሰችዉ መሆኑዋን ሊገባቸው ይገባል፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያን እንወዳለን የሚትሉ ነገር ግን በተግባር የኢትዮጵያን ብሔሮችን ለመጥራት እንኳን ቀፏችሁ አንኳስሳችሁ በ “ጎሳ” የተካችሁና በብሔራቸው ተደራጅተው በሀገር ውስጥና በሀገር ዉጭ በሰላማዊና መንገድና በነፍጥ የሚታገሉትን የሚትጎነትሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ቁጥር አንድ ጠላቶችና አፍራሽ አቋም አራማጆች እንደሆናችሁ ከወዲሁ አውቃችሁና እራሳችሁን አርማችሁ ተባብሮ በመስራት ኢትዮጵያን ከሚጠፉ ሀገራት (failed states) ተርታ እንዲትታደጓት ለማሳሰብ እወዳለው፡፡ካልሆነ ግን ጭቁኑን ህዝብና የምትፈልጉትን የጭቁኖችን መሬት ጭምር ሳትፈልጉት በግድ የሚትጋፈጡት የመለያየት አደጋ አንዳይሆን እሰጋለው፡፡

**ኢትዮጵያ በብሔሮች ስምምነት ትገንባ!!**

**Desalegn Mesa**

hawassasidama@gmail.com

**Hawassa, Sidama, Ethiopia**